ትችት

# ብሄራዊ ጥቅማችንን ማስቀደም ወይስ የኛ እያረበብን የሰው ማመስ?

ኤርትራ ከኢትዮጵያ በፖለቲካ የተገነጠለች ቢሆንም በኢኮኖሚ ከኢትዮጵያ የተለየች አይደለችም። እንዲያውም የኢሳያስ አፈወርቂ አገዛዝ በኢትዮጵያ ኪሣራ ራሱን ለማጠናከር የሚሰራ መሆኑን ብዙ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል።

በእርግጥ በሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች መሃከል ሊኖር የሚገባውን መረዳዳትና ትስስር የማይፈልግ ኢትዮጵያዊ የለም። ግን ይህ መረዳዳት በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተገነባ እንዲሆን ያስፈልጋል። እስካሁን በታየው ሁኔታ ግን ይህ ጨርሶ ተግባራዊ አይደለም።

ሌላው ይቅርና ኤርትራ ከኢትዮጵያ የምትገዛውን ቡና፣ የቅባት እህልና ቆዳ ወደ ውጭ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች። አንድ እግር ቡና ሳታበቅል ከዓለም በቡና ወደውጭ መላክ 14ኛ ቦታ መያዟ ብዙ ባእዳን ታዛቢዎችን ሳይቀር ያስገረመ እንግዳ ነገር መሆኑን ያየነው የሰማነው ነው። የምግብ እህል፣ አጠናና ነዳጅ ያለምንም ከልካየ ከኢትዮጵያ ትወስዳለች። ኢትዮጵያ ግን ከሷ የምታገኘው ተመጣጣኝ የሆነ ነገር የለም ምሁራኖቿ ሥራ እያጡ በሚንከራተቱባት ወይም ለስደት በሚዳረጉበባት አገር ኤርትራውያን ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣንና በንግዱ እንቅስቃሴም ውስጥ ዓይነተኛ ቦታ ይዘው ይሳተዳሉ። ኢትዮጵያውያን ግን በኤርትራ ውስጥ ተመሳሳይ እድል ማግኘቱ ይቅርና ለመኖር እንኳን ይቸገራሉ።

ይህ ሁሉ መዛባት በኢትዮጵያ መሪዎች ሳታይ ቀርቶ አይደለም። በማናቸውም ግንኙነት እነ አቶ አመለስን ማዘዝ የሚችለው የኤርትራ ገዥቡድን አሁንም እነ አቶ መለስ ብሄራዊ ጥቅማችንን አሳልፈው እንዲሰጡት እየተጫኑ ይገኛል።

የኤርትራ ገዥዎች የራሳቸውን ናቅፋ የተባለውን ገንዘብ ኢትዮጵያ ጋር ባላቸው የኢኮኖሚ ግንኙነት ሁሉ እንዲጠቀሙበት በይፋ ጥያቄ አቅርበዋል። ይህ ጥያቄያቸውም ተቀባይነት እንዳገኘ ይነገራል። ናቅፋ የተባለውን ገንዘብ እንደ ልብ እያባዙ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ በሰፊው ለመርጨትና የሃገራችንን ኢኮኖሚ ለማንኮታኮት እነ አቶ ኢሳያስ ዓይናቸውን ሳያሹ ያቀረቡትን ጥያቄ እነ መለስ ዜና ከተቀበሉት በሃንሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ቀውስ እንደሚከተል ግልጽ ነው። ዞሮ ዞሮ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያጋጥመውን የተባባሰ የኑሮ ቀውስና ጉስቁልና ከዚህ ዓይን ከወጣ ብዝበዛ ጋር ማገናኘቱ የማይቀር ስለሆነ ቁጣው ውሎ አድሮ እንደሚገነፍል ሳይታለም የተፈታ ነው።

ኢትዮጵያ በዚህ መልክ የምትዘረፈው ተረፉት እንዳይደለ ግልጽ ነው። 5 ሚልዬን የሚጠጉ ርሃብተኛ ልጆቿን ለመርዳት፣ በአዲስ አበባ ብቻ 6000ሺ ለሥራ የደረሱ ወጣቶቿን ከእንክርትና ከተስፋ ቢስ ኑሮ አላቃ ሥራ ለማስያዝ፣ ለፍቶ የሚያድረውን ድሃ ከተንጠለጠለበት የኑሮ ጠርዝ ለማላቀቅ፣ በመድሃኒትና በህክምና ተቋም እጦት በበሽታ ለሚረግፉ ዜጎቿ አገልግሎት ለመስጠት ... መዋል የሚገባው ጥሬ ሃብት ለኢሳያስ አፈወርቂ እንዲገብር መደረጉ ለነ አቶ መለስ ህልውና ይጠቅም እንደሆን እንጂ ከኢትዮጵያና ከህዝቧ ብሄራዊ ጥቅም አንጻር ሲታይ የራሷ ሲያርባት የሰው ታመሳለች የተባለው ዓይነት ቅጥ ያጣ እንቆቅልሽ እንደሆነ ግልጽ ነው።